# እውነትና ንጋት

በላቸው ታዬ

12-23-14

ኅዳር 17 ቀን 2007 ዓ.ም አዲስ ዘመን ጋዜጣ በአጀንዳ አምዱ "የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና ትክክለኛው ገፅታ" በሚል ርዕስ ባወጣው ሰፊ ፅሁፍ የድርጅቱን የትናንትና የዛሬ ጉዞ በንጽጽር በማሳየት፣ ችግሩን በመፈተሽ የማያሻማውን መፍትሄ አስቀምጧል፡፡ እውነቱንም ፍንትው አድርጎ አሳይቷል፡፡

ለድርጅቱ ፈጣን እድገት መጓተትና መዘግየት ትልቁና ማነቆው ችግር ከፍተኛው የውሣኔ ሰጪ አካል ቁርጥ ያለ ውሣኔ ለመወሰን አለመቻሉ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሙሉ በሙሉ በኮርፖሬት አወቃቀር ራሱን በራሱ ችሎ ገቢውንም ለራሱ አውሎ የተሻለ ገቢም አግኝቶ ሠራተኛውም በጥሩ ገቢ እንዲተዳደር አለማድረጉ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ አንጋፋ፣ በእድሜም ታላቅና ቀደምት መንግሥታዊ ተቋም ነው፤ ተገቢ ትኩረት በመንግሥት ስላልተሰጠውና በተለያዩ አደረጃጀት ውስጥ በማለፉ እየፋፋ ሳይሆን እየቀጨጨ እንዲሄድ የተደረገ ተቋም ነው፡፡

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በአንጋፋነት ጭርሱንም የማይወዳደሩ ጥቂት አሥርት ዓመታት እድሜ ብቻ ያላቸው ተቋማት በውስጥ አደረጃጀት፣ በተቋማዊ አቅምና የሰው ኃይል በዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችና በመሳሰሉት ልቀውና መጥቀው እንዲሄዱ ሲደረግ ለዚህ ድርጅት ተገቢ ትኩረት አልሰጠውም፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከ70 ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠረ፣ በተለያየ ዘመን አንቱ የተባሉ የሀገሪቱን አንጋፋና ስመጥር ጋዜጠኞች ያፈራ፣ በስሩም አዲስ ዘመን፣ ኢትዮጵያን ሔራልድ፣ በሪሣ፣ ለዓለምና ዘመን መጽሔትን ይዞ እየሰራ የሚገኝ ነው፤  ቀደም ሲል የነበረው ታሪካዊው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ በበጀት እጥረት እንዲዘጋ ተደርጓል፡፡ ይህም ውሣኔ ተገቢ አልነበረም፡፡

ይኸው ጋዜጣ ዛሬ ቢኖር የበለጠ ጠቀሜታ እንደነበረውም ለመካድ አይቻልም፡፡ ተፎካካሪ ሆኖ ሊወጣም ይችል ነበር፡፡ በመዘጋቱም የተገኘ ጠቀሜታ አለ ቢባል በጀት መቀነሱ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡

ይልቁንም አማራጭ ድምጽና የመረጃ ምንጭ በመሆን እያደገ ከመጣው የሕዝብ ብዛት ዘጠና ሚሊዮን ከመድረሳችንም አንጻር ጠቀሜታው የጎላ በሆነ ነበር፡፡ አንጋፋ ፕሬስ ከመሆኑ አንጻር የሀገሪቱን ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታና እድገት ተከትሎ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ለውጥና እድገት ለማሳየት በቻለና በጠቀመም ነበር፡፡ የፌደራሉ መንግሥት ይህንን በማመን ይህኑ የተዘጋ አንጋፋ የሀገሪቷን ጋዜጣም በአዲስ አደረጃጀት መመለስና ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግም አለበት፡፡

የትም ሀገር በእድሜ አንጋፋና ታላቅ የሆኑ ጋዜጦች የትውልድና የታሪክ ቅርስነታቸው እንዳለ ሆኖ ጋዜጦቹ የጊዜውን እውነት ተከትለው እንዲያድጉ ይደረጋሉ እንጂ አይዘጉም፡፡

ጋዜጣውን ለመዘጋት ያበቃው የፋይናንስ አቅም ማነስ ሲሆን ይህንንም በብዙ መልኩ መወጣት ይቻል ነበር፡፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ እንደ አዲስ ዘመንና ሌሎችም ሁሉ ለሀገሪቷም አስፈላጊዋ ነበር፡፡ የዛሬዋን ኢትዮጵያ በበለጠ መልኩ ለማሳየት በበቃም ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከኢህአዴግ በፊት 47 ዓመታት በኢህአዴግ ዘመን 23 ዓመታትን በተለያዩ ፈታኝ አደረጃጀቶችና መዋቅሮች አንዴ በአንዱ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሥር ሲሆን ሌላ ጊዜ በሌላ አደረጃጀት ተጠሪነት ሲኖረው ማዕበል እንዳንገላታው መርከብ በብርቱ አውሎ ነፋስና ወጀብ ወዲያና ወዲህ ሲዘም ብቅና ጥልቅ ሲል እንደበረሃዎቹ ግመል አርቢዎች ውኃና መኖ ፍለጋ እንደሚዞሩት ራሱ ቋሚ ቤትና አድራሻ ሳይኖረው ሠራተኛውም አመራሩም ሲንከራተት የኖረ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደምት ከሆኑት መንግሥታዊ ተቋማት በአንጋፋነቱ ከመጀመሪያዎቹ ተርታ የሆነ ሁሉም ያለፉ መንግሥታትም ሆነ አሁን ያለው የመኖሩን አስፈላጊነት በጥብቅ ያምናሉ፡፡ ሆኖም ግን ይህን የሀገር ቅርስ የሆነ

ተቋም ራሱን ችሎ በሁለቱ እግሩ እንዲቆም አላደረጉትም፡፡ ከጋዜጣና ከማስታወቂያ ሽያጭ በሚያገኘው ገቢ ራሱን ችሎ እንዲተዳደር አልተፈቀደለትም፡፡

ድርጅቱ በመንግሥት የበጀት ድጎማ በራሱ ገቢ የሚተዳደር ሆኖ ቀድሞ በገንዘብ ሚኒስቴር አሁን ደግሞ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያገኘውን ገቢ ያስገባል፡፡ ግማሹ የአስተዳደሩ ሠራተኛ በሲቪል ሰርቪስ ጋዜጠኛው ደግሞ በቦርዱ ይተዳደራል፡፡ በአንድ የመንግሥት ተቋም ውስጥ ይህ ዓይነቱ ጉራማይሌ አሠራር ለድርጅቱም እድገት ትልቅ ማነቆ ነው፡፡

ለድርጅቱ ፈጥኖ አለማደግ ዋናው ምክንያት ራሱን ችሎ በቦርድ እንዲመራና እንዲተዳደር የሚያገኘውንም ገቢ ሙሉ በሙሉ ለራሱ እድገት እንዲያውል አለመቻሉ ነው፡፡

እንዲያውም በቅርብ የኋላ ዓመታት የማተሚያ ዋጋ በመናሩ የተነሳ ጋዜጣና መጽሔቶች የሚታተሙበት ዋጋና ተሸጠው የሚያስገኙት ገቢ የሰማይና የምድር ያህል በመራራቁ ድርጅቱ መንግሥታዊ በመሆኑ እለታዊ ሕትመቶች መቋረጥ ስለሌለባቸው በዱቤ ለማሳተም የተገደደበት ደረጃም ላይ ደርሶ ነበር፡፡ ቢሆንም አሁን በሥራ ላይ ባለው ቦርድና ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ሠራተኛው ያላሰለሰ ትጋት በአጭር ጊዜ ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ የማተሚያ እዳውን ለብርሀንና ሠላም ድርጅት በመክፈል ራሱን ከእዳ አውጥቷል፡፡ ለዚያውም በየዓመቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ ማድረግ ያለበትን እያደረገ ማለት ነው፡፡

ይህ የሚያሳየው ድርጅቱ በነጻነት ራሱን በራሱ ቢያስተዳድር አቅሙን ፈጥኖ በማሳደግ ለሠራተኛውም የተሻለ ክፍያ በመስጠት የበለጠ ለውጥ እንዲመጣ ለማድረግ እንደሚቻል ነው፡፡ ከቀድሞው ያልተለወጠና ያልተሻሻለ የመንግሥት አሠራር በመቀጠሉ ድርጅቱ ራሱን ሙሉ በሙሉ ሊለውጥበትና ሊገነባበት የሚያስችለውን ትርፍ በሙሉ በየዓመቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማስገባቱን ቀጥሏል፡፡

ድርጅቱ ወደ ኮርፖሬሽን ደረጃ እንዲያድግ ጥናቱ ከተጠናቀቀ የቆየ ቢሆንም ወደ ተግባር ለመግባት ራሱን በራሱ ችሎ እንዲተዳደር ጉራማይሌው አሠራር ቀርቶ

በአንድ ወጥ እንዲመራ አስፈላጊ የሆኑት ተያያዥ ጉዳዮች እንዲሟሉለት የመጨረሻውን ውሣኔ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

ከዚህ ውጭ የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት፣ ሥራ አስኪያጁና አጠቃላይ ሠራተኛው የቱንም ያህል ቢሰሩም ለድርጅቱ እድገት ማነቆ የሆኑት መሠረታዊ ችግሮች መፈታት ካልቻሉ ወደሚጠበቀው ደረጃ መሸጋገር ያዳግታል፡፡

ቀድሞ የነበረውና 70 ዓመታትን የተሻገረው ችግር አለመፈታት ድርጅቱን በተፈለገው ፍጥነት ለማሳደግ ዘመናዊ አደረጃጀትና የሰለጠነ ብቁ የሰው ኃይል በብዛት እንዲኖረው ከሙያው ጋር ተያያዥነት ያላቸው የዘመናዊ የህትመት መሣሪያዎችና የራሱ ማተሚያ ቤት ባለቤት እንዲሆን የራሱ አማራጭ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው አላስቻለውም፡፡ ይህም የድርጅቱን ታላቅ የማደግ ተስፋ ያቀጨጨ ጉዞውንም የተፋጠነ ሳይሆን ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ ያደረገው አሠራር ነው፡፡

ውሣኔ ሰጪው መንግሥታዊው አካል አስተያየቶችን ከመስጠትና ይህ ቢደረግ ይህ ቢስተካከል ከማለት አልፎ ድርጅቱ በሁለት አወቃቀር በሲቪል ሰርቪስና በቦርድ ከመመራት ይልቅ ሙሉ በሙሉ ራሱን በራሱ ችሎ በአንድ ተጠቃሎ በቦርድ እንዲመራና በራሱ ገቢ እንዲተዳደር ቁርጥ ያለ ውሣኔ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይህን መወሰን ሲቻሉ ሠራተኛውም ጋዜጠኛውም በአጭር ጊዜ ድርጅቱን በማሳደግ ከፍተኛ ለውጥ እንደሚያመጣ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ይህን ውሣኔ ለመወሰን ቢቻል የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ቦርድ ማኔጅመንቱም ሆነ ሠራተኛውና ጋዜጠኛው በከፍተኛ ተነሳሽነት የላቀ ውጤትና እድገት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚያስመዘግቡ መናገር ይቻላል፡፡ ድርጅቱን ወደተሻለ ምዕራፍ ለማሸጋገር ኮርፖሬሽን ለማድረግ በሙያተኛ ተጠንቶ የተለያዩ ሀገራትም ልምድ ተካተዋል፡፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ በታሪኩ የመጀመሪያ በሆነ መልኩ ወደ ቀለም ሕትመት ተሸጋግሯል፡፡ ድርጅቱም የራሱ ዘመናዊ ሕንጻ ባለቤት ሆኗል፡፡

ይህ ውጤት የቦርዱ ሰብሳቢ፣ የቦርዱ አባላትና ሥራ አስኪያጁ፣ አስተዳደሩና የሠራተኛው፣ የጋዜጠኛውም የጋራ ልፋትና ድካም ውጤት ነው፡፡ በጥንካሬውም በድክመቱም የሁሉም የጋራና የተናጠል ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለበት፡፡

ውስብስብ የሆነውን የኢትዮጵያን ሚዲያ መንግሥታዊም ሆነ የግሉን ለመረዳት ሰፊና ጥልቅ የመስኩን እውቀትና ጥናት፣ ጥንትና፣ ትናንትን ዛሬን ፈትሾና አበጥሮ መረዳትን ማወቅን ይጠይቃል፡፡ ሀገራዊ እውነቱንና ጭብጡን ልዩ ባህሪያቱንም ለይቶ መገንዘብንም ግድ ይላል፡፡ በድርጅቱ ዙሪያ የሚሰነዘሩ አስተያየቶች የችግሩን ከፊል መፍትሄዎች ሊያመለክቱ ቢችሉ እንጂ ሙሉ መፍትሄ ያስገኛሉ ብሎ ማሰብም አይቻልም፡፡ የሚሰነዘሩት አስተያየቶችና በተጨባጭ በመሬት ላይ ያሉት እውነቶች አንድ አይደሉምና፡፡

አስተያየት፣ ትችት፣ ግምገማ ጠንካራና ደካማ ጎንን መለየት መፍትሄ ለማመላከት መቻል ራሱን ችሎ የሚደነቅና የሚበረታታ ቢሆንም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከሁለት መዋቅር እዝና አመራር ወጥቶ ራሱን በራሱ ችሎ ገቢውንም ለራሱ አውሎ ድርጅቱ እንዲለወጥና የሠራተኛውንም ችግር እንዲፈታ ወደ ላቀ ትርፋማነትና እድገት እንዲሸጋገር መወሰን ያለበት ዛሬ ነው፡፡ ዛሬ ነገ አይደለምና፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአምስት ዓመቱ መሪ የትራንስፎርሜሽን እቅድ መሠረት የተቀመጠውን አቅጣጫ በመከተል የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂክ እቅዶቹን ለማሳካት በትጋት ሰርቷል፡፡

የሀገሪቷን አንጋፋና እድሜ ጠገብ ጋዜጣ አዲስ ዘመንን በከፊል ቀለም ሕትመት ማሳተም መቻል፣ ድርጅቱ የራሱን ሕንጻ መሥራቱና ከኪራይ በመውጣት ማኔጅመንቱንና ሠራተኛውን በአንድ ላይ በማሰባሰብ ያልተሟላውን የድርጅቱን የሰው ኃይል የማሟላት ሥራ ከውኗል፡፡ ለውጥና እድገት ሂደት እንጂ በአንዴ የሚጨበጥ ባለመሆኑ ይኸውይቀጥላል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሀገሪቱን ልማትና እድገት ለሕዝቡ በማሳወቅና ተገቢ መረጃን በማድረስ ከሀገር ውስጥና ከውጭ የሚሰነዘሩ የጽንፈኛ ተቃዋሚ ቡድኖችን አፍራሽ ፕሮፓጋንዳና የፀረ ሠላም የአሸባሪና የአክራሪዎችን እኩይ ሴራዎች በማጋለጥና እርቃናቸውን በማስቀረት ረገድ በመጀመሪያው ግንባር በመሰለፍ አጋልጧል፡፡ ከፍተኛና ይህ ቀረሽ የማይባል ትንቅንቅና ተጋድሎም አድርጓል፡፡

ይህ የፀናና የማይናወጥ አቋም የሀገሪቱን ሠላም፣ አንድነት፣ ልማትና እድገት፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችን፣ የኃይማኖቶችን፣ የፆታዎችን እኩልነት በመጠበቅና

በማስከበር ረገድ የዚያኑም ያህል ፀረ ሠላምና ፀረ ልማት እንዲሁም ጽንፈኛና አክራሪ አሸባሪ ቡድኖችን ያለማሰለስ በማጋለጥ ዐቢይ ሙያዊ ድርሻውንም ተወጥቷል፡፡

ይህም ከየትኛውም መንግሥታዊ ተቋም በጎላ ሁኔታ በጽንፈኛው ተቃዋሚና በእስላማዊ አክራሪ ቡድኖች ዘንድ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በጋዜጦቹና መጽሄቶቹ ላይ የከፋ አፍራሽ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ በሀገር ውስጥና በውጭ ሚዲያዎቻቸው እንዲሁም ድረ ገፆቻቸው ለዓመታት እንዲያካሂዱ አድርጓቸዋል፡፡ ለዚህም ያለፉትን ሦስትና አራት ዓመታት የግል ፕሬስ ሕትመት የሆኑ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ ድረ ገፆች የፅንፈኛውን የራዲዮና ቴሌቪዥን ሥርጭቶች መመልከት ከበቂ በላይ መረጃ ይሰጣል፡፡ ዛሬም ይህ ሁኔታ ጋብ አላለም፡፡

ይህ ለዓላማ ጽናት፣ ለቁርጠኛ ሀገራዊ ልማትና እድገት ሠላም ለተደረሰበት ታላቅ ሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገትና እመርታዊ ለውጥ ቀጣይነት በግንባር የተከፈለ የማይናወጥ ፅናት ማረጋገጫ በመሆኑ ዛሬም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ የታላቅ ጥንካሬ መገለጫ እንጂ የድክመት ማሣያም አይደለም፡፡

የግንቦት ሰባት ልሣን የሆነው ኢሣት፣ የእነሱው የመረጃ ምንጮች እነ ሚኒሊክ ሣልሳዊ በጥላቻና በበቀል የተሞላ የስም ማጥፋት ዘመቻቸውን በፈጠራ አሉባልታና ወሬዎች በማጀብ ቀጥለዋል፡፡ በኪራይ ሰብሳቢ ሎሌዎችን በሆድ አዳሪነት አሰልፈው እንደሚጠቀሙባቸው የሚታወቅ ነው፤ እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉ የሚጋለጡበት ቀን ሩቅ አይሆንም፡፡

አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል ነው ነገሩ፡፡ በቃኝን የማያውቁ ኪራይ ሰብሳቢዎች የሚጋለጡት በራሳቸው ሥራ ነው፤ ለኢህአዴግም፣ ለሕዝብም፣ ለሀገርም፣ ለዴሞክራሲም፣ ለልማትም፣ ለሠላምም ታላቅ ጠንቅና አደጋ ናቸው፡፡

የመንግሥት ሚዲያው ትግል የሚያደርገው አስመስለውና ተመሳስለው ጭንብል አጥልቀው በመሀሉ ከሚገኙትና በውጭ ካሉትም ጽንፈኞች ጋር በመሆን በሥውር ከሚደልቁት፣ በዴሞክራሲ ስም ከሚነግዱት ሽቃጮች ጋርም በመሆኑ ትግሉ ውስብስብ የሚሆነውም ለዚህ ነው፡፡

ሌሎች መንግስታዊ የሚዲያ ተቋማት ባቀረቡት ጥናት መሠረት በቦርድ እንዲመሩና እንዲተዳደሩ፣ ገቢያቸውንም ለድርጅቱ እድገት እንዲያውሉ ሲወሰን ለምን ይህ ነጻነትና እገዛ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አልተሰጠም የሚለውን ጥያቄ በማንሳት የእርምት እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

ድርጅቱን ወደ ኮርፖሬሽን የማሳደጉ ጥናት ተጠናቆ አልቋል፡፡ ፕሬስ ድርጅት ለቢሮ አገልግሎት በወር አንድ ሚሊዮን ከሚከፍልበት ወጥቶ የራሱን ሕንጻ ሰርቶ ገብቷል፡፡ ሕንጻውን የማሟላቱ ሥራ በሂደት ይቀጥላል፡፡ ለውጥ ሂደት እንጂ የአንድ ጀምበርና የቀናት ሥራ አይደለም፡፡

የሀገሪቱ አንጋፋ የፕሬስ ተቋም የሆነው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአፍሪካ ካሉ ታዳጊ ሀገራት የመንግሥት ሚዲያ ተቋማትም እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንዲገኝ ያደረገው የራሱ ማተሚያ ቤት የሌለው በመሆኑ ነው፡፡

መንግሥት በሥሩ ካሉትና ከሚያስተዳድራቸው ማተሚያ ቤቶች አንዱን ወስኖ ከነሙሉ ድርጅቱና የሰው ኃይሉ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የኮርፖሬት አደረጃጀት ሥር እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የተለያዩ ሀገራት የፕሬስ አደረጃጀት የጋዜጣና መፅሔት ሕትመት፣ የማስታወቂያ ሥርጭቶችና ገቢ የየራሳቸው ማተሚያ ቤት ሁሉም ያላቸው ከመሆኑ ሌላ በተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን እንደሚከውኑ ይታወቃል፡፡

የሌሎች ሀገራት የፕሬስ ድርጅቶች ሥርጭታቸው በየዕለቱ በአየር በየብስ እንደሚካሄድ በየክፍላተ ሀገራቱ (በየክልል) ቅርንጫፍ ቢሮዎችና ማተሚያ ቤቶች እንዳሏቸው ጋዜጣና መፅሔቶች በእለታዊነት በዋና ከተማዋ ሲታተሙ በክልሎችም ኮፒዎቹ ተልከው የተወሰነ ኮፒ ታትሞ በተመሳሳይ ሰዓትና ቀን ለሕዝቡ እንደሚደርሱ የፕሬስ ድርጅቶቹ የተለያዩ የሕትመት ሥራዎችን በመስራት ተጨማሪ ገቢ እንደሚያገኙና የፋይናንስ አቅማቸው እጅግ ጠንካራ መሆኑን ለሠራተኛውም የተሻለ ክፍያ እንደሚከፍሉ ወዘተ...ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሙሉ ነፃነት ራሱን በራሱ ችሎ ገቢውንም ለራሱ አድርጎ እንዲሰራ ብሎም የተጣለበት የበጀት ገደብ እንዲነሳለት ቢደረግ በአጭር ጊዜ ድርጅቱ ታላቅ ለውጥ እንደሚያመጣ የታመነ ነው፡፡

ሠራተኛውም ጋዜጠኛውም እየለቀቀ ወደ ሌላ የመንግሥትና የግል ተቋማት የሚሄደው የተሻለ ደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ስለሚያገኝ እንጂ በድርጅቱ ውስጥ መሥራትን ጠልቶ ወይንም የአስተዳደር ችግር ስላለ አይደለም፡፡ 320 ከሚደርሱ የድርጅቱ ሠራተኞች ውስጥ ግማሹ በሲቪል ሰርቪስ ከፊሉ በቦርድ የሚተዳደርበት ጉራማይሌ አሠራር ተወግዶ ሙሉ በሙሉ በቦርድ እንዲመራ መወሰን አለበት፡፡

በድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች ላይ ያነጣጠረው የስም ማጥፋትና ማጠልሸት ዘመቻ በግንባር ቀደምትነት በፅንፈኛው አክራሪ ተቃዋሚ፣ በፀረ ፀላም አሸባሪ ቡድኖችና በተላላኪዎቻቸው የሚመራና የተቀነባበረ ለመሆኑ በገሀድ ይታወቃል፡፡ ሥርዓቱን ለመናድ አድብተውና ተመሳስለው የበግ ለምድ ለብሰው የሚገኙ ተኩላዎች ሥውር እጅና ደባ እንዲሁም አፍራሽ ተልዕኮ ያነገቡ ቡድኖች ተልዕኮ ይዘው ሰርገው በመግባትም እንደሚንቀሳቀሱ ይታወቃል፡፡

ይህ የጽንፈኛው አክራሪና የኪራይ ሰብሳቢዎች የተቀናጀ ሴራና ደባ እርቃኑን ወጥቶ የሚጋለጥበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡፡ በመንግሥታዊና በግል ተቋማት ውስጥ በመንሰራፋት ሚስጥራዊ የቃል ኪዳን ቀለበትም በማሰር የሀገሪቱን ፈጣን ግስጋሴና ልማታዊ እድገት በመመሳሰል ገብቶ የራስን ጥቅም በማሳደድ ለመክበር የሚቅበዘበዙ የጥገኛው የኪራይ ሰብሳቢዎች ቡድንና ስብስብ ቢሮክራሲውን ተገን በማድረግ የመንግሥት የሚዲያ ተቋማትንም እንዳያኮላሽና እንዳይበክል ብርቱ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ይታመናል፡፡

በሌላም ወገን ጽንፈኛው አክራሪ ተቃዋሚ ቡድን የራሱን ሰርጎ ገቦች በመንግሥት የሚዲያ ተቋማት ውስጥ ባሉ ጋዜጠኞች ውስጥ አስርጎ በማስገባት አመለካከትና አስተሳሰባቸውን ለመበከል የሚያደርገው ያላሰለሰ ጥረት የታወቀ በመሆኑ ይህንንም ፈጥኖ በመከላከል የእርምት እርምጃ በመውሰድ ማጥራት ለነገ የማይባል የቤት ሥራ ነው፡፡

በስም ማጥፋትና በአሉባልታ የታጀበና የተቀናበረ ዘመቻ የከፈቱት ኪራይ ሰብሳቢዎችና ጽንፈኛ ፖለቲከኞች መጨረሻቸው ውርደትና ውድቀት እንጂ ድል አይሆንም፡፡ እየታገሉ ያሉት ሥርዓቱን እንጂ ግለሰቦችን አይደለም፡፡

የድርጅቱን ግስጋሴ ለማጓተት የሚጥሩ ወገኖች ያላቸው ሥውር ተልዕኮ በግልጽ የሚታወቅ በመሆኑ ለድርጅቱ እድገትና ለተጀመረው ሀገራዊ የልማትና የስኬት ጉዞ በቁርጠኝነት የቆሙ ዜጎች ሁሉ ያለማሰለስ አበክረው ያታገሉታል፡፡

እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉም በራሳቸው አሳፋሪ ሥውር የተንኮል ሴራና ሸፍጥ ተጋልጠው እርቃናቸውን ይቀራሉ፡፡ ጉዞውም ያለማሰለስ ወደፊት ይቀጥላል፡፡